# ናዮሚ ክላይን ስትናገር ጆሮዎቻችን ሁሉ ሊቆሙ ይገባል



ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጨጭዋ ሕዝብዋ እንደ አሸዋ መበተኑ፣ የተሳቀቀ፣ እርስበርሱ የሚፈራራ፣ አበሳው የሚፈራረቅበት ሕዝብ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው? በእርግጥ በድህነት የተፈረጁ ሕዝቦች እውን ተስፋ ቢስ የሆነ አገር ውስጥ ነው የሚኖሩት ወይስ ሀብታቸውን እንዳይጠቀሙ ደንቃራዎች አሉባቸው? ስለምን ከርሰ ምድራቸው ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ያላቸው ሀገሮች ጦርነት ይበዛባቸዋል? ኢትዮጵያም ሆነች በርካታ ሌሎች አገሮች አስከፊ በሆነ አገዛዝ ስር ለአመታት የሚዳከሩት ጥሩ መሪ የሚሆን ሰው አጥተው ነው ወይስ እብሪተኛና ደንታ ቢስ አረመኔዎች ስልጣን እንዲይዙ ሀገራቸውን እየዘረፉ እንዲያዘርፉ አይዞአችሁ የሚላቸው ሀያል ኃይል ስላለ ነው? የበርሊን ግንብ መፍረሱን እናከብር በሚሉ መንግስታት ድጋፍ አዳዲስ ሀገር ከፋፋይ የሆኑ አጥሮች ዙርያችንን እየተገነቡብን አንድ የነበሩ ሀገሮች ዘጠኝ ትንንሽ እየሆኑብን አይደለምን? ኢትዮጵያውያን በነኒህ ጉዳዮች ላይ አበክረን ልንወያይና ከሀገራችን ችግር አኳያ አቅጣጫችንን ልንቀይስ ይገባል።

ናዮሚ ካላይን በሰሞኑ የአለማችን የአየር መዛባት ጉባዔ ሳቢያ አቶ መለስ የአፍሪካን ጥቅም የማያስጠብቅ ስራ መስራቱን አስመልክታ የዘገበችውን በኢትዮሚድያ ላይ ማንበቤ አስደስቶኛል። http://www.ethiomedia.com/course/4668.html

ናዮሚ ኢትዮጵያ ላይ ትኩረት መስጠትዋን ቀጠል አድርጋ የአቶ መለስ የክህደት ጉዞ መጀመርያውም መጨረሻውም ኮፐንሀገን አለመሆኑን በታዋቂው ብዕርዋ መጻፍዋን ትቀጥል ዘንድ ምኞቴ ነው።

ናዮሚ በጣም ተወዳጅ የሆኑ መጽሀፎችን የጻፈች ሲሆን በተለይ *The Shock Doctrine: The Rise of Disaster Capitalism* የሚለውን ማንበብ በመኪያሄድ ላይ የአለውን ግራ የሚያጋባ የራስን ሀገር የማጥፋት ዘመቻ ምንጭ ምን እንደሆነ ጥሩ ግንዛቤ ሊሰጠን ይችላል። ስለዚህ ሁላችንም ይህን መጽሀፍ ማንበብና ከዚያም አለፍ ብሎ በጋራ በመወያየት ከመጽሐፉ የምናገኘውን እውቀት መጋራቱ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ማስገንዘብ እወዳለሁ።




ናዮሚ ዘመናዊው ካፒታሊዝም በአደጋ (ጦርነትም ይሁን የተፈጥሮ) እንዴት እንደሚበለጽግ ነው ማስረጃዎች ያቀረበችው። የዚህ ፍልስፍና መሪ ደግሞ በ 2006 ዓም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ሚልተን ፍራይድማን የሚባል የቺካጎ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሲሆን አደጋ ትርፋማ መሆኑን እየገለጸ "የደነገጠ ወይም ሽብር ውስጡን ሰላም የነሳውም ይሁን አደጋ የደረሰበት፣ አጣብቂኝ ውስጥ ስለሚገባ ምርጫ አጥ ይሆናል። ያኔ ከፖለቲካ አንጻር ሊሆን ይችላል ተብሎ የማይታሰበው ሁሉ አይቀሬ ሆኖ ያርፈዋል" የሚለው እምነቱን ያስተማረ እናም በዚህ እኩይ እምነት ባተረፉት መካከል የተከበረ ሰው ነው።

*"Only crisis, actual or perceived, produces real change. When that crisis occurs, the actions that are taken depend on the ideas that are lying around. That I believe is our basic function: to develop alternatives to existing policies, to keep them alive and available until the politically unthinkable becomes politically inevitable."* Source: The shock doctrine page 7.

ናኦሜ በራስዋ አንደበት ስለመጽሀፉ የምትገልጸውን እዚህ መስማት http://www.youtube.com/watch?v=JG9CM_J00bw ይችላሉ። ስለዚህ በአፍሪካ በአየር መዛባት ምክንያት የሚደርሰው አደጋ ለሌሎች ከፍተኛ የገንዘብ ማግኛ ሊሆን ይችላል:: ችግሩ ሲበዛባቸው አፍሪካውያን አሁን አንቀው የያዙትን የተፈጥሮ ሀብት ለባለጠጎቹ አሳልፈው ይሰጡ ዘንድ ይገደዳሉ። በሱናሜ ምክንያት በተፈጠረው መፈናቀል ሳቢያ በውሀ ዳርቻ ላይ ያለው መሬት በመጤ ባለሀብቶች ተወርሶ አሁን አካባቢው የቱሪስት መናኸሪያ ሲሆን በዚያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ቤት የለሽ ተፈናቃይ ሆነዋል። በአሜሪካም በኒው ኦርሊንስ በካትሪና ጎርፍ የተፈጠረው መጥለቅለቅ አዲስና ነጻ መሬት እንዳስገኘ በመቁጠር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁኔታዎች ተለውጠዋል። ባለሀብት የሚባል ባልነበረበት ራሽያ ቦሪስ ሄልሲን ፓርላማውን በታንክ ባስከበበት ማግስት በ 'privatization' ስም በአንድ ጀንበር ሚሊየነሮች እንደጉድ ተፈልፍለዋል። ኤፈርትም በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የሌለው የንግድ ድርጅት በመሆን ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ በአንድ ጀንበር ሚሊየነር የሆኑ የወያኔ ባለስልጣኖች ሞልተዋል። አላሙዲ ከድሀ ሕዝብ መንጋጋ በሽያጭ ስም በተነጠቀ ሀብት ከአለም አርባ ሰባተኛው ባለጠጋ ሆነው ፍርፋሪ ለድሀው ጣል ጣል በማድረጋቸው አንቱም ዶክተርም ተብለዋል።

an impassioned,
wonderfully
y as hell. A
ınd anyone who
ıow the world
ıould read it

ሽፋን ላይ የሰፈረ

ወያኔዎች በታማኝ አነጋገር '**የማስጎንበስ ቴራፒ**' እያደረጉልን ነው። አንቀጥቅጠው፣ አዋርደው፣ ቁልቁል ደፍቀው እንዳቀረቀርን እንድንቀር ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ እያደረጉ ነው። ሲሻቸው በማሰር፣ በአደባባይ በጥይት ግንባር

እየሙቱ የደም ጎርፍ በማፍሰስ። ሀብት በመውረስ፣ በማዋረድ ሊታሰብ እንኳ የማይችለውን ወደ ተግባር ለውጠውታል። ይህን በመገንዘብ ከአንገታችን ቀና ለማለት ይቻለን ዘንድ ግራ ቀኙን እንመልከት። ናኦሜም በያዘችው መንገድ በመቀጠል በኢትዮጵያ እየሆነ ያለውን ትዘግብ ዘንድ የመረጃ ማቀበሉን፣ የማመስገኑንና የማበረታታቱን አስፈላጊነት ልጠቁምና መልካም ንባብ ልመኝላችሁ።

መልካም ጊዜ

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com